በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጴጥሮሳውያን
የቤተ ክርስቲያን ክብር እና መብት አስጠባቂ ኅብረት
Alliance of Petrosawian for the glory and right
of Ethiopian Orthodox Tewahedo Church

ቁጥር፡ ጴጥ 001/05/2012
ቀን 25/05/2012 ዓ.ም.

ለኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለሥልጣን

አዲስ አበባ

ጉዳዩ ፡- ኦ ኤም ኤን ቴሌቪዥን ጣቢያ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ላይ እያስተላለፈ ያለውን ሕገ ወጥ ሥርጭት ይመለከታል፡፡

የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለሥልጣን አግባብነት ባለው የሀገሪቱ የብሮድካስት አዋጅ አማካይነት ለብሮድካስት አገልግሎት ጣቢያዎች በሀገር ውስጥ መሥራት የሚያስችላቸውን ፈቃድ በመስጠት ከሥርጭት በኋላ ፕሮግራሞቻቸው የአገሪቱን ሕግ ማክበራቸውንና ኅብረተሰቡን የሚጎዳ ይዘት እንዳይተላለፍ በመቆጣጠር ላይ እንደሚገኝ ይታወቃል፡፡

ባለሥልጣኑ በሕጉ መሠረት የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ከሰጣቸው የቴሌቪዥን ጣቢያዎች መካከል አንዱ የሆነው የኦ ኤም ኤን ቴሌቪዥን (Oromiya Media Network) ጥር 9 ቀን 2012 ዓ.ም በሥርጭት ላይ ባዋለው ፕሮግራም ኦሮሞ ፌዴራላዊ ኮንግረንስ (**ኦፌኮ**) የተባለ የፖለቲካ ፓርቲ በኦሮሚያ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን ፍቼ እና ገርበ ጉራቻ /ኩዩ/ ከተሞች ያደረገው ሕዝባዊ **የምርጫ ቅስቀሳ አስተላፏል፡፡** በወቅቱም አቶ ኃይለ ሚካኤል ታደሰ የተባሉ ግለሰብ በምርጫ ቅስቀሳው ላይ ያስተላለፉት መልእክት በቀጥታ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ላይ ያነጣጠረ፣ ከሕገ መንግሥቱ እና ከአገሪቱ የምርጫ ሕግ በተጻራሪ በቤተ ክርስቲያናችን ላይ የተደረገ የጥቃትና ጠብ አጫሪ ቅስቀሳ ከመሆኑ ባሻገር ምእመናንን የሚከፋፍል፣ ስም የሚያጠፋና በሐሰት የሚወነጅል ድርጊት ነው፡፡

በመሆኑም የቴሌብዥን ጣቢያው ይህንኑ ቅስቀሳ በቀጥታ ቀርጾ በሥርጭት ላይ በማዋሉ ፕሮግራሙ ከተላለፈበት ዕለት ጀምሮ ይልቁንም ከሁለት ቀናት በኋላ በተከበረው ዓለም አቀፍ በሆነው የጥምቀት በዓል ላይ ምእመናን እና አገልጋዮች ላይ እንዲሁም የበዓሉ የአከባበር ሥነ

Scanned by CamScanner

ሥርዓት ላይ የጥቃት ዘመቻ እንዲከፈት አስተዋጽኦ አድርጓል። በዚህም ሕዝቡ ተረጋግቶ ሃይማኖታዊ ሥርዓቱን ማክበር እና መፈጸም እንዳይችል የተደረገ ከመሆኑም በላይ ብዙዎች ለሕይወት ህልፈት፣ ለአካል ጉዳት፣ ለንብረት ውድመት ብሎም ለስደት/መፈናቀል/ እንዲጋለጡ አድርጓቸዋል።

ይህ ጠብ አጫሪ፣ ከፋፋይ፣ በሐሰት የሚወነጅል፣ በሕዝቦች መካከል ጥላቻን የሚዘራና በመላ አገሪቱ በምእመናን መካከል ሁከት የሚፈጥርና የማምለክ ነጻነትን የሚጋፋ ሃይማኖታዊ ጉዳይን ለምርጫ ፖለቲካ ፍጆታ ያዋለ ሕገ ወጥ ንግግር ከተሰራጨ በኋላ እስከ አሁን ድረስም በአካባቢውም ሆነ በተለያዩ ቦታዎች በከተማም ሆነ በገጠር ምእመናን እና አገልጋዮች በስጋት እና በሰቀቀን እየኖሩ ይገኛሉ።

በብሮድካስት አገልግሎት አዋጅ ቁጥር 533/199 በአንቀጽ 7(5) ባለ ሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ***"ሕገ ወጥ ሥርጭቶችን በሚመለከት ቁጥጥር ያደርጋል"*** ሲል ይደነግጋል፤ እንዲሁም በአዋጁ አንቀጽ 30/4/ሀ - ሠ በተቀመጡት ድንጋጌዎች መሠረት ***"ለሥርጭት የሚቀርብ ፕሮግራም የሌሎችን እምነት የማያንኳስስ፣ የግለሰብን፣ የብሔር ብሔረሰብን፣ የሕዝብን ወይም የድርጅትን ስም የማያጠፋ ወይም በሐሰት የማይወነጅል፣ ብሔረሰብን ከብሔረሰብ የማያጋጭ፣ ወይም በሕዝቦች መካከል የእርስ በርስ ግጭት የማያነሳሳ ወይም ጦርነት የሚቀሰቅስ መሆን የለበትም"*** የሚለውን ፍጹም በመጻረር ቅስቀሳቸውን አከናውነዋል። በወቅቱም አቶ ኃይለ ሚካኤል ታደሰ የተባሉ ግለሰብ በሰሜን ሸዋ ፍቼ እና ገርበ ጉራቻ /ኩዩ/ ከተሞች ኦሮሞ ፌደራላዊ ኮንግረንስ (ኦፌኮ) በተባለ የፖለቲካ ፓርቲ ሕዝባዊ የምርጫ ቅስቀሳ ላይ የተናገረው እና OMN ቴሌቪዥን በሥርጭት ላይ ያዋለው ፕሮግራም የብሮድካስት አዋጅን፣ የምርጫ ሕጉንና በተለይም ሕገ መንግሥታዊ መብታችንን የተጋፋ በመሆኑ በሕጉ መሠረት አስተማሪ እርምጃ እንዲወሰድ እየጠየቅን ለአብነት ግለሰቡ በምርጫ ቅስቀሳው ላይ በኦሮምኛ ቋንቋ ከተናገሯቸው አደገኛ ንግግሮች መካከል በጥቂቱ እንደሚከተለው ዘርዝረናል:-

- እናንተ የኦሮሞ ወጣቶች /ሰላሌዎች/ በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንግዶች ሆናችኋል ለምንድን ነው እንግዶች የሆናችሁት?
- ደብረ ሊባኖስ የእናንተ ነው፤ ካሁን በኋላ ደብረ ሊባኖስ ላይ የምታዙት እናንተ ናችሁ
- ከአሁን በኋላ በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ላይ የምታዝዙት እናንተ ናችሁ
- ወደ ቤተ ክርስቲያን ሰብራችሁ ግቡ እና **ግቡ ከእጃቸው ተቀበሉዋቸውና እጃችሁ** አስገቡ
- በሃይማኖት የምትከፋፍለን ቤተ ክርስቲያን አንፈልግም

Scanned by CamScanner

- **ኦሮሞን በጎሳ የምትከፍል** ቤተ ክርስቲያን አንፈልግም
- **ዶ/ር ብርሃኑ ነጋን መስቀል አሳልማ ፐ/ር መራራ ጉዲናን የምታገል ቤተ ክርስቲያን አንፈልግም**
- በሌሎች መርሐ ግብር ላይ ተገኝታ የጃዋርን መርሐ ግብር የምትጠላ ቤተ ክርስቲያን አንፈልግም
- ቄሮ ቀሬ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንግዳ አልሆናችሁም? በቋንቋችሁ እያመለካችሁ ነው? በቋንቋችሁ እየቀደሳችሁ ነው? የኦሮሞ ቄስ፣ ዲያቆን፣ ጳጳስ አገልጋይ አልናፈቃችሁም?
- በቤተ ክርስቲያን ላይ እንደባዳ እንደ ሽፍታ አልታያችሁም ይህ ከአሁን በኋላ መቆም አለበት
- **እኛ ሰላሌ ላይ ቤተ ክርስቲያንን ነጻ ማውጣት አለብን**

በተጨማሪም ግለሰቡ ቤተ ክርስቲያንዋን በሐሰት በመወንጀል፣ ስም በማጥፋት ከገለፀበት አገላለጽ መካከል

- የፖለቲካ ኢምባሲ መፍረስ አለበት
- የፊውዳሎች የፖለቲካ ኤምባሲ መፍረስ አለበት
- የቀድሞ ሰዎች የፖለቲካ ኢምባሲ መፍረስ አለበት በማለት የተናገራቸውን የሁለቱን ከተሞች ቅስቀሳ OMN ቴሌቪዥን በሥርጭት ላይ አውሏቸዋል

OMN ቴሌቪዥን ባሰራጨው ፕሮግራም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ክብር እና ልዕልና የሚጋፋ ከመሆኑም በላይ ዓለም አቀፋዊትና ኩላዊት የሆነችውን ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ባለቤትነት ለተወሰኑ ቡድኖች የሚሰጥ ነው፡፡ በዚህም ሌላውን እንደምታገልና ሕዝብን በጎሳና በሃይማኖት ከፋፋይ እንደሆነች አድርጎ በማቅረብ ሌሎች የተገፉና የተገለሉ እንደሆኑ ይገልጻል፡፡ **"ቤተ ክርስቲያንዋ አግልላችኋለች"** ያላቸውን ቡድኖች **ቤተ ክርስቲያኒቱን ሰብረው እና ገፍተው እንዲገቡና ሌሎችን ከቤተ ክርስቲያን እንዲያስወጡ የተደረገው ቅስቀሳ በቀጥታ በቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን በሀገር ውስጥ አመጽና ብጥብጥን የሚፈጥር** ነው፡፡ በተለይ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን እና አገልጋዮችዋን እጅግ የከፋ አደጋ ላይ የሚጥልና ለጥቃት ያጋለጠ ሁኗል፡፡ በውጤቱም በሰሞኑ በሀገሪቱ ውስጥ የቤተ ክርስቲያኒቱን ምዕመናንን እየለዩ እየተፈጸሙ ያሉ ልዩ ልዩ ግጭቶችና አደጋዎች ማሳያ ናቸው፡፡

በአጠቃላይ የሃይማኖትን ጉዳይ ለምርጫና ፖለቲካ ቅስቀሳ ማዋል የአገራችንን **የምርጫ** እና ሌሎች ሕጎችን የሚጻረር በመሆኑ በብሮድካስት አገልግሎት ተቋማት ተዘጋጅተው **የሚቀርቡ**

Scanned by CamScanner

ወይም የአየር ሽፋን የሚሰጣቸው ዝግጅቶች ስጋትን፣ ሽብርን፣ የርስ በርስ እልቂትን ሳይሆን ተስፋን፣ ሠላምን፣ መከባበርን በአገራችን በጎ እሴት በታቀኘ መልኩ ለአድማጭ ተመልካች ማድረስ የመገናኛ ብዙኃን ኃላፊነት በመሆኑ ባለስልጣኑ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ሕገ መንግሥታዊ እና ተቋማዊ ነጻነታችን እንዲሁም የምዕመናንን እና በአጠቃላይ የሀገራችን ሕዝቦች መብት በሚዲያ እንዳይጣስ ጥብቅ ክትትል እንዲደረግ እንጠይቃለን።

በመጨረሻም OMN የተባለው የሚዲያ ተቋም በተደጋጋሚ ጊዜ የሕግ ጥሰቶች ሲፈጸም የብሮድ ካስት ባለሥልጣን እርምጃ ይወስዳል በሚል ሕዝበ ክርስቲያኑ ሲጠብቅ የነበረ ቢሆንም በባለሥልጣኑ በኩል ምንም ዓይነት የእርምት እርምጃ ባለመወሰዱ የተፈጠረብንን ቅሬታ እንገልጻለን። OMN ቴሌቪዥን የብሮድካስት አገልግሎት አዋጁን እና ሌሎቹንም ሕጎች በተጻረረ መልኩ በሥርጭት ላይ ባዋለው ፕሮግራም ሳቢያ በኢትዮጵያ ኦ/ተ/ቤ/ን ላይ ለተፈጸመው እና እየተፈጸመ ላለው አደጋ እንዲሁም በኦርቶዶክሳዊነቱ የማይደራደረውን የቤተ ክርስቲያኒቷ አማኝ የሆነውን የኦሮሞ ሕዝብ ያሳዘነ አጥፊ ለሆነ ተግባር ሁሉ ጣቢያው ቀጥተኛ ተጠያቂ ነው። በመሆኑም ባለስልጣኑ አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት ጉዳዩን መርምሮ ቴሌቪዥን ጣቢያው ቤተ ክርስቲያንን በይፋ ይቅርታ እንዲጠይቅ እንዲሁም ላሰራጨው የጥፋት አዋጅ ግልጽ ማስተባበያ እንዲሰጥ እንዲደረግ እንጠይቃለን። ወደፊትም ጣቢያው ከመሰል ሕገ ወጥ ተግባራት እንዲቆጠብ በባለሥልጣን መሥሪያ ቤታችሁ በኩል ማስጠንቀቂያ እንዲሰጠውና አፈጻጸሙም ክትትል እንዲደረግበት እንጠይቃለን።

እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ

መጋቤ ብርሃናት ቀሲስ ሙሉቀን ብርሃኑ
የኅብረቱ ሰብሳቢ

ግልባጭ፡-

- ለጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት
- ለኢፌዲሪ ሰላም ሚኒስቴር
- ለኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት
- ለኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን
- ለኢትዮጵያ ሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ
- ለብሔራዊ መረጃ እና ደኅንነት አገልግሎት
- ለቅዱስ ሲኖዶስ ጽ/ቤት
- ለመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት
- ለሰላም እርቅ እና አንድነት ዐቢይ ኮሚቴ

አዲስ አበባ

Scanned by CamScanner